# ከእነ ዶ/ር አምባቸው መኮንንና ከእነ ጀኔራል ሰዓረ መኮንን ግድያ ጋር በተያያዘ 13 ግለሰቦች ክስ ተመሰረተባቸው።

November 22, 2019

ከሰኔ 15ቱ ጥቃት ጋር በተያያዘ የተጠረጠሩ 13 ግለሰቦች ክስ ተመሰረተባቸው

(ኤፍ ቢ ሲ) በባህርዳርና አዲስ አበባ ከአማራ ክልል አመራሮችና ከእነ ጀኔራል ሰዓረ መኮንን ግድያ ጋር በተያያዘ በወንጀል ድርጊቱ "እጃቸው አለበት" በሚል የተጠረጠሩ 13 ግለሰቦች ክስ ተመሰረተባቸው።



የጀኔራል ሰዓረ ጥበቃ የነበረው አስር አለቃ መሳፍንት ጥጋቡ፣ የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ /አብን/ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ክርስቲያን ታደለን ጨምሮ 13ቱም ተከሳሾች በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርበው ክሱ ተነቦላቸዋል።

ዓቃቤ ህግ በተከሳሾቹ ላይ "ህገ መንግስትን በኃይል ለመናድ ተንቀሳቅሰዋል" በሚል ክስ መስርቶባቸዋል።ተከሳሾቹ በማረፊያ ቤት የደህንነት ስጋት አለብን በሚልም ለችሎቱ ያቀረቡ ሲሆን፥ በምርመራ ወቅት የተወሰዱባቸው ንብረቶች እንዲመለሱላቸው መጠየቃቸውን ከኢቢሲ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

ተከሳሾቹ ለቀረበባቸው ክስ የመቃወሚያ ምላሻቸውን ለታህሳስ 1 ቀን 2012 ዓ.ም እንዲያቀርቡ ችሎቱ ውሳኔ ያሳለፈ ሲሆን፥ ከደህንነት ጋር ላነሱት ጉዳይ በማረሚያ ቤት ሆነው ጥብቅ ጥበቃ እንዲደረግላቸውም አዟል።

ለምርመራ በሚል ስለተወሰዱባቸው ንብረትም በዝርዝር ለችሎቱ እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ አስተላልፏል። ተጠርጣሪ ተከሳሽ አስር አለቃ መሳፍንት ችሎቱ የሚጠይቀውን ምላሽ መስጠት እንዳልቻለና እሺ እና አዎ የሚሉ ምላሾችን ብቻ መስጠቱም ታውቋል።

ችሎቱም መናገር ካልቻልክ ሀሳብህን በፅሁፍ ግለፅ ማለቱንና ተከሳሹ ይህንንም አለመቻሉ ተመልክቷል።

ከሰኔ 15ቱ ጥቃት ጋር በተያያዘ ባህርዳር ላይ የአማራ ክልል አመራሮች ዶክተር አምባቸው መኮንን፣ አቶ ምግባሩ ከበደና አቶ እዘዝ ዋሴ ሲገደሉ፥ አዲስ አበባ ላይ ደግሞ የኢፌዴሪ መከላከያ ኃይል ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጀኔራል ሰዓረ መኮንንና ሜጀር ጀኔራል ገዛኢ አበራ መገደላቸው ይታወሳል።